# መሠረተቢስ ሪፖርት ይብቃን

## ክፍል ሁለት

ኢ.ብሳ ነመራ 03/25/14

በዚሁ ርዕስ በቀረበ ክፍል አንድ ፅሁፍ ላይ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ ያወጣው ሪፖርት ሰብአዊ መብትን በማስከበር ረገድ የኢትዮጵያ መንግስት ያለውን ቁርጠኝነት፣ በዚህ ዙሪያ እስካሁን ያከናወናቸውን ተግባራትና ያገኛቸውን ውጤቶች የዘነጋ መሆኑን ተጨባጭ እውነታዎችን በማንሳት ተመልክተናል። በዚህ በክፍል ሁለት ፅሁፍ ደግሞ የሪፖርቱን ይዘት ዋና ዋና የሆኑ ትችቶችን በመጥቀስ ለመመልከት እሞክራለሁ።

በሪፖርቱ ላይ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተብሎ ከቀረበውና ብዙዎችን ግራ ካጋባው፣ ካስገረመውም ልጀምር። በሪፖርቱ ክፍል ስድስት **“በጾታዊ ዝንባሌ፣ በፆታዊ ማንነትን መሰረት በማድረግ የሚፈፀሙ ማህበራዊ ጫናዎች፣ መድልዎና ጥቃት”** በሚል ርዕስ ስር የቀረበው ነው። “በአገሪቱ የወንድና የሴት ግብረ ሰዶማውያን፣ እንዲሁም ፆታቸውን የቀየሩ ሰዎች ላይ ከሚፈፀም ጭቆና የሚከለክል ህግ የለም” ይላል። በእንደነዚህ አይነት ሰዎች ላይ የኃይል ጥቃት ሲፈጸም፣ መገለልንና ሌሎች ጫናዎችን በመፍራት አቤቱታ እንደማያቀርቡ የገለፀው የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሪፖርት፣ “የግብረሰዶማውያንና ፆታቸውን የቀየሩ ሰዎች አመለካከት አራማጆች ክትትል እንደሚደረግባቸውና ለደህንነታቸው እንደሚፈሩ ጠቁመዋል” ይላል።

እርግጥ ነው አሜሪካ የዚህ አይነት ከተፈጥሯዊ ፆታዊ ዝንባሌ ውጭ ለሆኑ ሰዎች ሕጋዊ እውቅና ሰጥታ ሊሆን ይችላል። ተመሳሳይ ፆታ ያላቸው ሰዎች በአሜሪካ ጋብቻ እስከመፈፀም መብት ተሰጥቷቸው ሊሆን ይችላል። ይህ የአሜሪካ ባሕልና ሥነምግባር እንዲሁም ማህበራዊ ፍልስፍና የፈቀደው ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለኝ።

ኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን ለወንድና ሴት ግብረሰዶማውያን የሕግ እውቅና አልተሰጠም። ይህ ድርጊት እስከሚታወቀው ድረስ ከሰው ተፈጥሯዊ ፍላጎትና ዝንባሌ ውጭ በመሆኑ የኢትዮጵያውያን ሥነምግባር ይፀየፈዋል። በኢትዮጵያውያን አመለካከት፣ ሰብአዊ

መብቶች ከሰው ተፈጥራዊ ፍላጎቶች - ሰብአዊ ፍላጎቶች ብቻ የሚመነጩ ናቸው የሚል እምነት በመኖሩ፣ በኢትዮጵያ እስካሁን ባለወ ነባራዊ ሁኔታ  ከዚህ ውጭ ለሆኑ ፍላጎቶች የሕግ እውቅና መስጠት አስፈላጊ ነው የሚል እምነት የለም። ይህ ህብረተሰቡ ውስጥ ያለ ገዢ አመለካከት ነው። ሕጎች ከማህበረሰቡ ባህልና የሥነምግባር ደንብ እንደሚመነጩም መታሰብ አለበት። ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ግብረሰዶማዊነት አለ የሚባልበት ደረጃ ላይ አልደረሰም። ከቅርብ ግዜ ወዲህ ጭምጭምታ የሚሰማ ቢሆንም፣ እነዚህም ከውጭ አገር በተለይ ከአሜሪካ የግብረሰዶማዊነትን ምግባር ወርሰው በተመለሱ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ዘንድ የተወሰነ ነው። እርግጥ እነዚህ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወደሌሎቹም ያዛመቱበት ሁኔታ የለም፣ የመስፋፋት አዝማሚያ አይታይበትም ማለት አይቻልም፡፡ ያመ ሆነ ይህ (ከሕዝቡ የሚነሳው ከፍተኛ ተቃውሞ እንደተጠበቀ ሆኖ) ሕግ ማውጣት እስከሚያስፈልግ ድረስ እንደ አንድ የማህበረሰብ ቡድን አልተስፋፋም።

እናም የአሜሪካ የውጭ ገዳይ መስሪያ ቤት ኢትዮጵያ  "ለወንድና ሴት ግብረሰዶማውያን እንዲሁም ፆታቸውን ላስቀየሩ ሰዎች የሕግ ዕውቅናና ድጋፍ አልሰጠችም" በሚል እንደሰብአዊ መብት ጥሰት የቀረበው ውንጀላ የህብረተሰቡን ገዢ አመለካከትና ባህል/ሥነምግባር እንዲሁም ሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎች ያላገናዘበ መሰረተ ቢስ ነው። ሌሎች ጉዳዮችም ላይ የቀረቡት ትችቶች ከዚህ የተለዩ አይደሉም።

ሌላው በሪፖርቱ ላይ የቀረበውና፣ ብዙዎችን "የሚያቀርቡትን አጥተው ነው" ያሰኘው ሪፖርቱ የባለፈው የፈረንጆች ዓመትን ማለትም የ2013ን የሰብአዊ መብት አያያዝ የሚመለከት ሆኖ ሳለ፣ ከሶስት አመት በፊት በፈረንጆች አቆጣጠር በ2010 የተካሄደውን 4ኛውን ዙር አገራዊ ምርጫ የሚመለከት ጉዳይ  ነው። ይህ ጉዳይ በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሪፖርት እንደአዝማች በተደጋጋሚ የቀረበና ከበቂ በላይ መልስ የተሰጠበት በመሆኑ መልሶ መልስ መስጠት አላስፈላጊ ብቻ ሳይሆን እንደሞኝነት የሚቆጠርም በመሆኑ እተወዋለሁ። የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱን ግን ሳንታዘበው አናልፍም።

ሪፖርቱ ከዚህ በፊትም በተደጋጋሚ ሲያቀርበው የቆየውና ምናልባት እንደማድመቂያ ጌጥ የቆጠረው የሚመስለው "በተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና በጋዜጠኞች ላይ አስር ይፈፀማል" የሚለውን ዘንድሮም አውጥቶታል። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት " ዘንደሮ ደግሞ

እነማን ታሰሩ ?” ተብሎ ቢጠየቅ እነዛኑ የዛሬ ሶስት አመትም ከጠቀሷቸው የታቃዋሚ ፓርቲ አባላትና “ጋዜጠኞች” ውጭ መጥራት እንደማይችሉ እርግጥ ነው።

እነዚህ በተደጋጋሚ የሪፖርት ማድመቂያ የሆኑት ጋዜጠኛና ፖለቲከኛ ተብዬዎችም ቢሆኑ፣ የተከሰሱትና ቅጣት ተወስኖባቸው የታሰሩት  በዘፈቀደ አለመሆኑ ወይም በያዙት ፣ በፃፉት ወይም በተናገሩት ሃሳብ አለመሆኑ በተደጋጋሚ ተነግሯል። ሰዎቹ በቁጥጥር ስር የዋሉትና የተከሰሱት፣ የቅጣት ውሳኔ የተላለፈባቸው በአገሪቱ ሕጎች ላይ ወንጀል ተብለው የተደነገጉ ድርጊቶችን ፈፅመው በመገኘታቸውና ይህም ለፍርድ ቤት በቀረበ ማስረጃ በመረጋገጡ ነው። “ስራቸው ጋዜጠኛ የሆኑት ሰዎች ላይ በፍርድ ቤት ክስ መመስረቱና የቅጣት ውሳኔ መተላለፉ ተገቢ አይደለም” የሚል አቋም ካላቸው ጥፋተኝነታቸውን ለማረጋገጥ የቀረቡት ማስረጃዎች ላይ ነው ማተኮር የነበረባቸው። ማለትም ጥፋተኛ ያሰባላቸውን ማስረጃዎች የሚያፋልስ ማስረጃዎችን ነው ማቅረብ የነበረባቸው። በዚህ ዓመት በወጣው ሪፖርት ላይ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ቀደምም በወጡት ሪፖርቶች ላይ ይህ ተደርጎ አያውቅም። ይህ ትችቱን መሰረተ ቢስ ያደርገዋል።

የአሜሪካ የውጥ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሪፖርት ከዚሁ ከፕሬስ ነፃነት ሳይወጣ፤ “በሕትመት ሚዲያው ላይ ገደቦች ተጥለዋል” ይላል። የዚህን ወቀሳ መሰረተ ቢስነት ብዙም ሳንሄድ፣ የግል ጋዜጦችና መፅሄቶችን የሚሸጡና የሚያነቡ ኢትዮጵያውያንን በተለይ የአዲስ አበባና የሌሎች ትላልቅ የአገሪቱ ከተሞች ነዋሪዎችን በማነጋገር ማረጋገጥ ይቻላል። አንዳችም ገደብ አልተደረገባቸውም፡፡ እንደውም የፕሬስ ነፃነትን ላለመገደብ ባለ ፍላጎት ህግ ሲጥሱ ሁሉ በትእግስት የሚታለፉበት ሁኔታ ነው ያለው።

በተለይ በየሳምንቱና በየሁለት ሳምንቱ የሚወጡ ከውጭ የገንዘብ ድጋፍ ይደረግላቸዋል የሚባሉ  መፅሄቶች ላይ የሚወጡ ፅሁፎችን በቅንነት የተመለከቱ ብዙዎች “በዚህ አገር ሕግ የለም ወይ?” ብለው እስከመጠየቅ የደረሱበት ሁኔታ ነው የሚስተዋለው። መፅሄቶቹ በግልፅ የአመፅ ቅስቀሳ የሚያካሂዱ፣ ሽብርተኝነትን የሚያበረታቱ ፅሁፎችን ይዘው መውጣታቸው መለያ ባህሪያቸው ለመሆን በቅቷል። እናም የሕትመት ሚዲያው እንኳን ገደብ ሊደረግበት ሕግን ተላልፎ ሰላማዊ ዜጎች ላይ ስጋት እየፈጠረ ነው። የእነዚህ የፕሬስ ውጤቶች ጋዜጠኞችና አዘጋጆች የአመፅ ጥሪ እየለፈፉ ሰላማዊ ዜጎችን እያሸማቀቁ ነው።

ለዚህ አስረጅነት ሪፖርቱ በተደጋጋሚ “ጫና ተደርጎበታል” እያለ የሚያወራለት ተመስገን ደሳለኝ የተባለው ጋዜጠኛ የሚያዘጋጀው “ፋክት” የተሰኘው መፅሄት ላይ የወጡ አንድ ሁለቱ ፅሁፎች ላይ የሰፈሩትን ሃሳቦች ልጥቀስ ።

ፋክት መፅሄት በታህሳስ 2006 ዕትሙ “ሕዝባዊ ብሶት የከተማ አብዮት?” በሚል ርዕስ ባሳተመው ፅሁፍ፤

*ኢህአዴግ ለአስራ ሰባት አመት አስከፊ መስዋዕትነትን ከፍሎ የመሰረተው መንግስት ከመንግስቱ ኃ/ማርያም አስተዳደር ያለው ልዩነት የስም ብቻ ነው። እኛም የለውጥ መንገድ ለመፈለግ ፊታችንን ወደ አውሮፓውያኑ የ”ብርቱካናማ” እና የ”የጽጌረዳ” አሊያም ወደ አረቡ የ”ፀደይ” አብዮት እንመለስ ዘንድ ያስገድደናል።*

*የከተማ ተቃውሞ የጠመንጃውን ያህል ባይሆንም እንኳ ዋጋ ማስከፈሉ አይቀሬ መሆኑ ግን መዘንጋት የለበትም። አደባባዩን ከማማተር አስቀድሞ አብዮቱ መያዝ የሚገባው ባሕሪ ማስታወስ ያስፈልጋል። ይህም የትኞቹንም ጨቋኝ ህጎች በአደባባይ መጣስ ነው። ለምሳሌ ‘እዚህ ቦታ ለመሰለፍ ጠይቀን ተከለከልን ደጋፊዎቻችንን እንዳንሰበስብ አዳራሽ አጣን’ እና መሰል ቀልዶችን በመተው አዋጆቹን (እንደፀረ ሽብር እና የፕሬስ አዋጅ ውስጥ ያደፈጡ ቀፍዳጅ አንቀፆችን) በግላጭ በመጣስ በገፍ ወደዘብጥያ ለመውረድ መወሰን . . .”*
የሚል ሃሳብ አስነብቧል።

በየካቲት 2006 ዕትሙ “የፈራ ይመለስ” በሚል ርዕስ ባቀረበው ፅሁፍ ደግሞ፤

*. . . ጀግኖች አባቶቻችን ላለፉት ሦስት ሺህ ዓመታት ለነፃነታቸው ሲዋደቁ ኖረዋል። በውጤቱ ነፃ ሃገር አስረክበዋል። ይሁንና ዛሬም እኛ ዘመነኛ ትውልድ “ነፃነት” እያልን የምንጮህበት ይህ ክቡር ጉዳይ ገና ምላሽ አላገኘም። እርግጥ ጥያቄው ከባዕድ ወረራና ተወራሪ ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡ ከሃገር ልጆች ጭቆና እንጂ።*
የሚል ሃሳብ አስፍራል።

እነዚህን ሁለቱን በቅርብ ስላገኘኋቸው ለአብነት ያህል ጠቀስኳቸው እንጂ የፋክትና የመሰሎቹ ጋዜጦች ላይ ዘውትር የመወጡ ፅሁፎች የእነዚህ አይነት አመፅ ቀስቃሽ ይዘት ያላቸው ናቸው።

እነዚህ ሁለት "ፋክት" ከተሰኘ መፅሄት ላይ የተቀነጨቡ ፅሁፎች ሃሳቦች ሕገመንግስታዊ ስርአቱን ለመናድ የተላለፉ ግልጽ የአመፅ ቅስቀሳዎች ናቸው፡፡ ወጤቱ አገር የሚያጠፋም ቢሆን ሕገመንግስታዊ ባልሆነ መንገድ ሥርአቱን መናድ አስፈላጊ መሆኑን የሚሰብኩና ለዚህ የሚቀሰቅሱ ሃሳቦች ናቸው፡፡ የመፅሄቱ አዘጋጆች ግን በእነዚህና በመሰል በርካታ ፅሁፎቻቸው አልተጠየቁም፡፡ መንግስት ይህን ያህል ሆደ ሠፊ የሆነው ለፕሬሰ ነፃነት መጎልበት ባለው ጉጉት ነው። ሌሎች በሚዲያው ላይ ያሉ ሰዎች እንዳይሸማቀቁ ለማደረግ ነው፤ በቃ። ይህ ዕውነታ ባለበት ሁኔታ "ሚዲያው ላይ ገደብ ተጥሏል" የሚል ትችት መሰንዘር የሚያስተዛዝብ ነው።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪየ ቤት ሪፖርት የሰብአዊ መብት ተሟጋች ነን ባዮቹ አምነስቲ ኢንተርናሽናልና ሂዩማን ራይት ዎች በተደጋጋሚ እንዲሚያደርጉት "በኢትዮጵያ በማህበር የመደራጀት መብት ላይ ገደብ ተጥሏል" ይላል። ይሁን እንጂ ለዚህ ወቀሳ አስረጂነት አንድም በማህበር መደራጀት የተከለከለን ግለሰብ በዋቢነት አቅርበው አያውቁም። ከዚህ ይልቅ ከአራት አመት በፊት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፀደቀውን የሲቪክ ማህበራትና በጎ አድራጎት ድርጅቶች አዋጅ ነው የሚጠቅሱት።

በመሰረቱ በዚህ አዋጅ ላይ መደራጀት አልተከለከለም። ቀደም ሲል ከነበረው የማህበራት ምዝገባ የተለየ ነገር ቢኖር ከ10 በመቶ በላይ የገንዘብ ምንጫቸው ከውጭ የሆኑ ማህበራት እንደውጭ ድርጅት/ማህበር ይመዘገባሉ የሚለው ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የውጭ አገር ማህበራት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ እንደማይገቡም ተደንግጓል። ልብ ባሉ የውጭ ሲቪክ ማህበራትና በጎ አድራጎት ድርጅቶች ኢትዮጵያ ውስጥ መንቀሳቀስ አልተከለከሉም። በማንኛውም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ያለገደብ መንቀሳቀስ ይችላሉ። የፖለቲካ ጉዳይ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያን ብቻ በመሆኑ እዚህ ውስጥ ግን መግባት አይችሉም። በመሆኑም ገደቡ መቀመጡ አስፈላጊ ነው።

ኢትዮጵያውያን ያቋቋማቸው የሲቪክ ማህበራት ግን ምንም ገደብ የለባቸውም። የፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጥም መግባት ይችላሉ።

የውጭ ሲቪክ ማህበራት በአንድ ሉአላዊ አገር ፖለቲካ ውስጥ መግባታቸው የሚያስከትለውን መዘዝ በቅርቡ በዩክሬን የተካሄደውን ሕገወጥ የመንግስት ለውጥ በማየት መረዳት ይቻላል። የዩክሬኑን ሕገወጥ የመንግስት ለውጥ የመሩት የአሜሪካ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መሆናቸውን ልብ በሉ። እስካሁን እልባት ያላገኘውንና ደም አፋሳሹን የግብፅና የሶርያ የመንግስት ለውጥ እንቅስቃሴም በእነዚሁ የአሜሪካ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተጠነሰሱና የተመሩ መሆናቸውንም ማስታወስ ተገቢ ነው።

አዋጁ ማህበራት እንዳይመዘኑና እንዳይንቀሳቀሱ አንዳችም ገደብ አላደረገም፡፡ ለዚህ አስረጂነት አዋጁ ከወጣ በኋላ የተመሰረቱትንና የተመዘገቡትን ድርጅቶችና ማህበረት እንዲሁም ያደረጉትን እንቅስቃሴ መጥቀስ ይቻላል። አዋጁ በ2001 ዓ.ም ፀድቆ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ባሉት ሶስት አመታት ብቻ ከ1ሺ.ህ በላይ አገር በቀል ሲቪል ማህበራት ተደራጅተው ተመዝግበዋል። የፖለቲካ ተሳትፎን በተመለከተ፣ አዋጁ ከወጣ በኋላ በ2002 ዓ.ም በተካሄደው 4ኛ ዙር አገራዊ ምርጫ ላይ ከ10 ሚሊዮን ህዝብ በላይ የሚወክሉ አስራ ሁለት የአገር ውስጥ ሲቪል ማህበራት በመላው አገሪቱ በእያንዳንዱ የምረጫ ጣቢያ ታዛቢዎች ልከው የምረጫውን ሂደት ታዝበዋል። ከዚህ የተለየ የመደራጀትና የፖለቲካ ተሳትፎ የማድረግ መብትና ነፃነት ምን አይነት ይሆን?

በመሆኑም የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሪፖርት ከመደራጀት መብት ጋር አያይዞ የሰነዘረው ትችት መንግስትን ከሕዝቡ ፍላጎት ውጭ እጅን መጠምዘዝ የሚችልበት መንገድ ስለተዘጋ የቀረበ እንጂ ከሰብአዊ መብት ጋር የሚያገናኘው አንዳችም ነገር የለም። እንዲያውም "ዜጎች በውክልና ስልጣን የሰጡትን መንግስት በማስወገድ ሰብአዊ መብታቸውን የምጥስበት መንገድ ለምን ተዘጋብኝ" ከሚል ለቅሶ የተለየ አይደለም።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በሪፖረቱ "መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ገብቷል" ብሏል ። በተለይ በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ መግባቱን ነው ያመለከተው። በኢትዮጵያ መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸው ተደንግጓል።

የሕገመንግስቱ አንቀጽ፣ 11 “ መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፤ ምንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።” ይላል።

መንግስት በሃማኖት ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ የማይገባው የአሜሪካ መንግስት ወይም ሌላ ሰብአዊ መብት ተሟጋች ቡድን “በሪፖርት ይተቸኛል” ብሎ ሳይሆን በሕዝብ የስልጣን ውክልና ሲወስድ ሕገመንግስቱ ለማስከበርና ለማስከበር ቃል ስለገባ ነው። እስካሁን መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ አልገባም። የአሜሪካ የውጥ ጉዳይ መስሪያ ቤትም ሆነ ሌሎች መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ መግባቱን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ አይችሉም።

በሕገመንግስቱ መሰረት መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባት የሌለበትን ያህል ሃይማኖትም በመንግስት/ በፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ የመግባት መብት የለውም። ይሁን እንጂ በተለያዩ አገራት አክራሪዎች ሲያደርጉ እንደቆዩት፣ ሙስሊም አክራሪዎች በሃይማኖት ሽፋን የፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ የገቡበት ሁኔታ በተጨባጭ ታይቷል። ከዚህ በተጨማሪ ስውር የፖለቲካ አላማቸውን ለማሳካት ከአንድ ዓመት በላይ ለሚሆን ግዜ ሙስሊሞች የፀሎት ስርአት በሚከወኑባቸው ስፍራዎች ረብሻ በማንሳት ሰላማዊ የፀሎት ስርአት አውከዋል።

እነዚህ ድርጊቶች የሕገመንግስትና ሌሎች ከሕገመንግስቱ የመነጩ ህጎች ጥሰቶች ናቸው። መንግስት የሕገ መንግስትና የሌሎች ሕጎች ጥሰት ሲፈፀም የማስከበር ሕገመንግስታዊ ግዴታ አለበት። በመሆኑም በሃይማኖት ሽፋን ስውር የፖለቲካ አጀንዳ የሚያራምዱና በሃይማኖት ተቋማትና በሌሎች የአምልኮ ስፍራዎች ሰላማዊ የፀሎት ስርአቶችን ያወኩ ግለሰቦች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ተገቢና ተመጣጣኝ ሕጋዊ እርምጃ ወስዷል። ይህ ሕገመንግስት የማስከበር እንጂ በሃይማኖት ጣልቃ የመግባት እርምጃ አይደለም።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ ገብቷል ለሚለው አስረጅነት “በኢድአልፈጥር በአል ላይ ከ1ሺህ በላይ ሰዎችን ለአጭር ጊዜ በቁጥጥር ስር አውሏል፣ የተወሰኑት በቁጥጥር ስር እያሉ ሕይወታቸው አልፏል” ብሏል።

የ2005 ዓ/ም የኢድ አል ፊጥር በአል የፀሎት ስርአት ላይ ሥውር የፖለቲካ አጀንዳ ባላቸው አክራሪዎች የተመለመሉ ጀሌዎች ሰላማዊ የፀሎት ስርአቱንና የአዲስ አበባ ከተማን ሰላማዊ እንቅስቃሴ የሚረብሽ ሁከት ለመቀስቀስ መሞከራቸው ይታወቃል። በዚህ ወቅት አዋኪዎቹ ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ አድማ የመበተን ስራ ተሰርቷል። አድማ በመበተን ሂደት የአክራሪው ቡድን ጀሌዎች በተለያየ ቦታ ለሰአታት እንዳይንቀሳቀሱ ተደርጓል። በአንዳንድ አካባቢዎች ለሰአታት እንዳይንቀሳቀሱ የቆዩባቸው ስፍራዎች የፖሊስ ጣቢያዎች ነበሩ። ይህ አዋኪዎቹን ለሰኣታት እንዳይንቀሳቀሱ ማድረግ የአድማ ብተና የስራ ሂደት አካል እንጂ ሰዎችን በእስር እንደማቆየት ሊወሰድ የሚችል አይደለም።

ሪፖርቱ አይን ያወጣ ውሸትም ተካትቶበታል። ይህም "በኢድ አልፈጥር በአል ላይ በቁጥጥር ስር ከዋሉ ሰዎች መሃለል የሞቱ ሰዎች አሉ" ተብሎ የቀረበው ነው። በዛን እለት ለሰአታት በቁጥጥር ስር ከቆዩ ሰዎች መሃከል የአንድም ሰው ሕይወት አላለፈም። በቁጥጥር ስር ከቆዩት መሃከል ወደ ቤታቸው ከሄዱም በኋላ የሞተ እንደሌለ መረጃዎች ያመለክታሉ። የአሜሪካ መንግስት የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት "የኢትዮጵያ መንግስት በሙስሊሞች ላይ ግድያ ፈፅሟል" የሚለውን አክራሪው ቡድኑ ለስውር የፖለቲካ ዓላማ ማሳኪያው የፈበረከውን ውሸት እንደወረደ ተቀብሎ ቸክችኮታል። ይህ በጣም አሳፋሪና ሃላፊነት የጎደለው ተግባር ነው።

"ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮች ስልኮቻቸውና ሌሎች የኤልክትሮኒክስ መገልገያ መሳርያዎቻቸው ይጠለፋል የሚል ጥርጥር አላቸው" የሚል ውንጃላም በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሬፖርት ላይ ወጥቷል። ይሄም የተቃዋሚዎች የተለመደ መሰረተ ቢስ ውንጀላ ነው። የኢትዮጵያ ሕገመንግስት አንቀፅ 26 ቁጥር 1 ላይ፣ "ማንኛውም ሰው በግል የሚፅፋቸውና የሚፃፋቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌ ኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም " ይላል። በዚሁ አንቀፅ ቁጥር 2 ላይ ". . .አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሄራዊ ደህንነትን፣ የህዝብን ሰላም፣ ወንጀልን በመከላከል፣ ጤናንና የህዝብን የሞራል ሁኔታ በመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነቶች በማስከበር ዓላማዎች ላይ

በተመሰረተ ዝርዝር ሕጎች" በቁጥር አንድ ላይ የሰፈረው ድንጋጌ ሊገደብ እንደሚችል ይገልፃል።

በመሆኑም በዚህ መሰረት የተጠቀሱትን ወንጀሎች ሊፈጽሙ ይችላሉ የሚል በቂ ግምት ሲኖር በፍርድ ቤት ውሳኔ የሰዎች ስልኮችና ሌሎች የኤልክትሮኒክስ መገልገያ መሳርያዎች የሚጠለፍበት ሁኔታ አለ። ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጭ የማንም ስልክ ወይም ሌላ የኤሌክትሮኒክስ መልዕክት ማስተላለፊያ መሳሪያ አይጠለፍም። በመሆኑም ተቃዋሚዎቹ ሃሳባቸውን ስለሚያውቁት ይህ እያባነናቸው ስልካቸው የተጠለፈ መሰሏቸው ይሆናል እንጂ ምንም የተፈፀመ ነገር የለም። ማስረጃም አላቀረቡም። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያቤትም ይህን ውንጀላ ሲያቀርብ አንዳችም ማስረጃ አላቀረበም።

ከዚህ ውንጃላ ጋር በተያያዘ አሜሪካ የሉአላዊ አገር መሪዎችን ጭምር የስልክ ልውውጥ በመጥለፍ የምትታወቅ ሆና ሳለ፣ ኢትዮጵያ ይህን ነገር መፈፀሟን የሚያሳይ አንዳችን ማስረጃ ሳይኖር ለመተቸት መነሳቷ ብዙዎችን አስገርሟል። ይህ ድርጊት የሰብአዊ መብት ጥሰት መሆኑን ካወቀች ከራስዋ መጀመር ነበረባትና።

ሪፖርቱ እንደሰብአዊ መብት ጥሰት ካነሳቸው በርካታ ጉዳዮች መሃከል የሪፖርቱን መሰረተቢስነት የሚያሳይ አንድ ልጨምርና ፅሁፌን ላጠቃል። ሪፖርቱ "የትምህርት ነፃነት" በሚለው ርዕስ ስር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የ70:30 የተፈጥሮ ሳይንስና የማህበራዊ ሳይንስ የቅበላ ጥመርታን እንደ መብት ጥሰት አቅርቦታል።

ትምህርት ቅንጦት አይደለም። ሰዎች ተፈጥሯዊና ማህበራዊ አካባቢዎችን እንዲረዱ፣ ለሕይወት ፍላጎት ግብአት ሊሆን በሚችሉበት መንገድ መለወጥ፣ ስርአት ማስያዝ የሚያስችል ስርአት ያለው እውቀት ነው። ዕውቀት ሰዎች በሕይወት መኖር የሚያስችላቸው፣ ሃብት በማፍራት የህይወት ዋስትናቸውን ማረጋገጥ የሚያስችላቸው፣ ፍትህና ሰላም ማስፈን የሚያስችላቸው መሳሪያ ነው፡፡ ጉልበት ነው ማለት ነው።

እናም ሰዎች በሕይወት ለመኖር፣ የመኖር ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ እውቀት ያስፈልጋቸዋል። አገርም የሰው ሀብቷን ተጠቅማ በእድገት የሕዝቧን ኑሮ ወደተሻለ ደረጃ

ለማሸጋገር ዕውቀት የታጠቀ የሰው ኃይል ያስፈልጋታል። በመሆኑም ስርዓተ ትምህርት ቀርፆ ዜጎችን ማሰልጠን የመንግስት ሃላፊነት ነው።

በዚህ መሰረት ከእያንዳንዱ ግብር ከፋይ ኢትዮጵያዊ በሚሰበሰብ ገንዘብ በተገነቡትና በሚንቀሳቀሱት፣ብቃት ላላቸው ዜጎች በነፃ የትምህርት አገልግሎት በሚሰጡ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ሰልጥነው የሚወጡ ሰዎችን የእውቀት ስብጥር የአገሪቷ እድገት ከሚፈልገው የሰው ኃይል ጋር መጣጣም አስፈላጊ ነው። የ70 በ30 የተፈጥሮ ሳይንስና ምህንድስና እና የማህበራዊ ሳይንስ ጥመርታ መነሻ ይህ ነው። ሌላው መታወቅ ያለበት ተማሪዎች በዚህ ጥመርታ መሰረት የመማር ግዴታ የለባቸውም። ከዚህ ጥመርታ ውጭ ተማሪዎችን በሚቀበሉ የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመማር ዕድላቸው ክፍት ነው። እንግዲህ ይህ በምን አግባብ ነው እንደሰብአዊ መብት ጥሰት የሚቆጠረው?

በአጠቃላይ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የ2013 የሰብአዊ መብት ሪፖርት ላይ ኢትዮጵያን በሚመለከት የሰፈረው በተጨባጭ መረጃ ያልተደገፈ፣ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ፣ የመንግስትን ገፅታ ለማቆሸሽ በሚፈልጉ ወገኖች የተቀነባበረ፣ ለወደፊት መንግስት የሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ ያለውን ብቃት ማጎልበት እንዲችል የማያግዝ መሠረተቢስና የፈጠራ ወሬ ነው። መሠረተቢስ የፈጠራ ሪፖርት ይብቃን።